# የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ አመራሮችና ሰራተኞች የውጪ ህክምና መመሪያ ቁጥር 445/2013

ኢትዮጵያ አለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ የተቀመጡ መብቶችን የሚፈፅም፤ለስደተኞች የተሻለ ከለላ የሚሰጥና ለችግሮቻቸው ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኙ የሚያስችል በአለም አቀፍ መመዘኛዎች መሰረት የተቀረጸ ተቋም እንዲኖራት በማሰብ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይን ራሱን ችሎ በኤጀንሲ ደረጃ በአዋጅ 1097/2011 እንዲቋቋም ያተደረገ በመሆኑ በኤጀንሲው ቁመና አመራር ተመድቦ እየሰራ ያለ በመሆኑ፤

በሀገሪቱ ያለው የውጪ ምንዛሬ ወጥነት የሌለው እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ያለ በመሆኑ፤

የኤጀንሲው አመራሮችና ሰራተኞች የውጪ ህክምናን የሚመለከቱ በስራ ላይ ያለው ህግ ተግብራዊ በሚደረግበት ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት ለአገልግሎት ተጠቃሚው የተሻለ አሰራር በመዘርጋት የኤጀንሲውን ቁመና በሚያንፀባርቅ መልኩ የአመራሮችና ሰራተኞች የውጪ ህክምና መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤ የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ “ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ አመራሮችና ሰራተኞች የውጪ ህክምና መመሪያ ቁጥ 445/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2.ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ  አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. ኤጀንሲ  ማለት የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ ማለት ነው

2. ከፍተኛ አመራር ማለት ዋና ዳይሬክተር ጀነራሉ እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር ጀነራሎች ማለት ነው፤

3. ሰራተኛ ማለት ከዳሬክቶሬት አመራሮች ጀምሮ ያሉ ሁሉም ቋሚ ሰራተኞች ማለት ነው

4. የውጪ ህክምና ማለት ከኢትዬጵያ ውጪ የሚደረግ ህክምና ማለት ነው

5. ማናጅመንት ማለት የኤጀንሲው የበላይ ስራ አመራር የማናጅመንት ኮሚቴ ማለት ነው

6. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በመላው የአጀንሲው አመራርና ቋሚ ሰራተኛ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

### 4.የአገልግሎቱ ጥያቄ አቀራረብ እና አተገባበር

1.ማንኛውም የውጪ ህክምና አገልግሎት ፈላጊ የፈለገውን አገልግሎት በፅሁፍ ለከፍተኛ አመራሩ ማቅረብ አለበት

2.የቀረበለት አመራር ለማናጅመንቱ ውሳኔ በማሰጠት መልሱን ለአገልግሎት ፈላጊው በአጭር ቀናት ማሳወቅ አለበት

3.አገልግሎት ጠያቂው ህክምናው የተፈቀደለት ከሆነ በኤጀንሲው ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች አገልግሎቱን የማሳለጥ ግዴታ ይኖራቸዋል

### 5.በህክምናው የሚሸፈኑ ወጪዎች እና የኖቱ አይነት

1.የህክምናው ወጪ ኖት በአሜሪካን ዶላር ምንዛሬ የሚሸፈን ይሆናል

2.ለከፍተኛ አመራር የውጪ ህክምናው ወጪ ሙሉ በሙሉ በኤጀንሲው ይሸፈናል፤

3.ከህክምናው ወጪ ውጪ አገልግሎቱ የተሰጠው ከፍተኛ አመራር በህክምናው ወቅት ለሚያጋጥመው ወጪ የአልጋ እና የምግብ ወጪ በቀን 250(ሁለት መቶ ሀምሳ) ዶላር ለ10(አስር)ቀናት ኤጀንሲው ይሸፍናል

4.አገልግሎቱ ለተሰጠው ከፍተኛ አመራር ኤጀንሲው የትራንስፖርት ወጪ በወቅቱ ዋጋ ደርሶ መልስ ትራንስፖርት ይሸፍንለታል

5.አገልግሎቱ የተፈቀደለት ሰራተኛ የህክምና ወጪ 10(አስር ሺ)ዶላር ድረስ በወቅቱ የዶላር ምንዛሬ በኤጀንሲው ይሸፈናል

6.ከህክምናው ወጪ ውጪ አገልግሎቱ የተሰጠው ሰራተኛ በህክምናው ወቅት ለሚያጋጥመው ወጪ የአልጋ እና የምግብ ወጪ በቀን 150(አንድ መቶ ሀምሳ) ዶላር ለ10(አስር)ቀናት ኤጀንሲው ይሸፍናል

## 6.በአንድ የበጀት አመት የሚፈቀደው የውጪ ህክምና

1.በአንድ የበጀት አመት ውስጥ ለአንድ የውጪ ህክምና አገልግሎት ጠያቂ የሚፈቀደው ለሁለት ዙር መብለጥ አይችልም

## 7.ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 1.ስለተሻሩ ህጎች

ከዚህ በፊቱ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር የተሻሻለ የልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅም አሰጣጥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 01/2010 በሚለው አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2፣3፤እና 4 በዚህ መመሪያ ተሽሯል

## 2.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በዳይሬክተር ጀነራሉ ከተፈረመበት ከታህሳስ 20 ቀን 2012 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡